# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 171133

ታኅሣስ 22 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡-አቶ ደመቀ አየለ - አልቀረቡም ከተባለ በኋላ ጠበቃ መሰለ ገ/ጊዮርጊስ ቀረቡ

ተጠሪ፡-የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የብስክሌት ባለቤት ከዉል ዉጭ ኃላፊ የሚሆንበትን አግባብ በሚመለከት የቀረበዉን ክርክር ተከትሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ የቀረበ ክርክር የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ስልጣን ባየዉ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ከክርክሩ እንደተረዳነዉም ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበዉ ክስ የአሁን አመልካች ንብረት የሆነ ብስክሌት የደንበኛዩ ንብረት የሆነዉን የሰሌዳ ቁጥሩ 3-28392 ኦሮ የሆነዉን ተሽከርካሪ በቆመበት በመግጨት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርዮአረጋጋምዓለማአየገለግልም!

የኋላ መስታወት፣ የኋላ ፓራዉልት፣ የግራ የኋላ መስታወት እና የዝናብ መጥረጊያ ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ዉጪ በመሆኑ ብር 29,478.25 ወጪ በማድረግ የደንበኛዉን ተሽከርካሪ ጨረታ አዉጥቶና አወዳድሮ ማስጠገኑን በመግለጽ አመልካች ብር 29,478.25 ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ ሲል ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የአሁን አመልካችም በአንድ ሳይክል አንድ ግዙፍ መኪና በደረሰ ግጭት ደረሰ የተባለዉ ጉዳት ከህሊና ግምት ዉጪ በመሆኑ ፕሮፎርማም የተሰበሰበዉ ከአንድ ጋራዥ ብቻ በመሆኑ ተጋኖ የቀረበ ስለሆነ አግባብነት እንደሌለዉ፤ተሽከርካሪዉ ለሚያደርሰዉ ጉዳት ባለቤቱ ኃላፊነት ያለበት ቢሆንም ብስክሌቱን ሲያሽከረክር የነበረዉ ሽመልስ አማረ የተባለዉ ግለሰብ መሆኑ እየታወቀ የብስክሌቱ ባለቤት ጥፋት እንደፈጸሙ በማስመሰል ክስ መቅረቡ ተገቢ አይደለም ተብሎ ዉድቅ እንዲደረግላቸዉ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየዉ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብስክሌቱን ሲያሽከረክር ነበር የተባለዉ ግለሰብ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ትእዛዝ ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም የአሁን አመልካች መጥሪያ ለማድረስ ባለመቻላቸዉ አሽከርካሪዉ ጣልቃ እንዲገባ የሰጠዉን ትእዛዝ በማንሳት የአሁን ተጠሪ ምስክር ባለመቁጠሩ የአሁን አመልካች የቆጠሩትን አንድ ምስክር በመስማት በተጠሪ ደንበኛ ተሽከርካሪ ላይ ጉዳት ያደረሰዉ የአመልካች ብስክሌት እንደሆነና ተሽከርካሪዉን ለማስጠገን የአሁን ተጠሪ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ወጪ ማድረጉን ከቀረበዉ ክርክርና ማስረጃዎች ማረጋገጡን በመግለጽ የአሁን አመልካች ብር 29,478.25 ከ9% ሕጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍሉ በመ/ቁጥር 0125071 ላይ በቀን 29/10/2010 ዓ/ም ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዉ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 02-19550 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ የአሁን አመልካች በብስክሌታቸዉ በተጠሪ ደንበኛ ተሽከርካሪ ላይ የደረሰዉን ጉዳት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2081 መሰረት የመካስ ኃላፊነት አለባቸዉ በማለት በቀን 17/04/2011 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ የስር ፍርድ ቤቱን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡አመልካች በቀን 12/06/2011 ጽፈዉ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በዚህ መልኩ በተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

ንብረትነቱ የአመልካች የሆነ ጉዳት ያደረሰዉ ብስክሌት በሰዉ ኃይል የሚነዳ በቁመትም ሆነ በክብደት ትልቅ የሆነዉን ኃይሩፍ ተሽከርካሪ ገጭቶ በክሱ የተጠቀሰዉን ያህል ጉዳት ያደርሳል ተብሎ እንደማይገመት፤ ጉዳቱ ሊደርስ የቻለዉ በቢስክሌቱ ኃይል ምክንያት እንደማይሆን ግምት መዉሰድ ሲገባ መታለፉ አግባብ እንዳልሆነ፤ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2081 መሰረት ኃላፊ የሚሆነዉ ጉዳቱን ያደረሰዉ ባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም መኪና ባለቤት የሆነ ሰዉ ሆኖ እያለ ብስክሌት በሰዉ ኃይል የሚነዳ እንጂ ባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም መኪና ባልሆነበት በዚህ ድንጋጌ መሰረት

ኃላፊ ነህ ተብሎ ካሳ እንዲከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ ተብሎ እንዲታረም በመጠየቅ አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት የሰበር አቤቱታ እና በስር ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ መርምሮ ተጠሪ በደንበኛዉ ተሽከርካሪ ላይ የደረሰዉን ጉዳት በማስጠገን አወጣሁኝ ያለዉ ገንዘብ አስመልክቶ አመልካች ጉዳቱ የደረሰዉ በሞተር ሳይሆን በብስክሌት በመሆኑ ካሳዉን መክፈል ያለበት ብስክሌቱን ሲያሽከረክረ የነበረዉ ግለሰብ እንጂ ባለቤት ኃላፊ ሊሆን አይገባም ሲሉ ያቀረቡት ክርክር ዉድቅ የመደረጉን አግባብነት ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2081/1 ትክክለኛ አተረጓጎም አንጻር ለማጣራት መዝገቡ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በቀን 20/08/2011 ዓ/ም የተጻፈ መልስ በማቅረብ ብስክሌቱ የአመልካች መሆኑ መረጋገጡን፤ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2081/1 ባለሞተር ተሽከርካሪ የሚል ቢሆንም ይህ አንቀጽ በራሱ እነዚህ ብቻ ናቸዉ (exhaustive) በሚል ያላስቀመጠ በመሆኑ ከአንቀጹ መረዳት የሚቻለዉ ዝርዝሩ ዉስጥ ሌሎች ተሽከርካሪዎች ሊካተቱ እንደሚችሉ (illustrative እንደሆኑ) ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን ብቻ ያካትታል ብሎ መተርጎም ተገቢ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የደረሰቡት ድምዳሜ ተገቢ ነዉ፤ይህ ከታለፈም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2086/1 መሰረት ብስክሌቱ ባለሞተር ባይሆንም በፋብሪካ ተመርቶ የወጣ በመሆኑ አመልካች በዚህ ድንጋጌ መሰረት ኃላፊነት ስላለባቸዉ የሰበር አቤቱታዉ ዉድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

አመልካችም በቀን 30/08/2011 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል ከያዘዉ ጭብጥ አንጻር ከግራ ቀኝ ክርክር፣ከክልሉ ፍርድ ቤቶች ዉሳኔዎች እና አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ ከክርክሩ እንደተረዳነዉ ንብረትነቱ የአመልካች የሆነ ብስክሌት በሌላ ሰዉ እየተነዳ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-28392 ኦሮ የሆነዉን የተጠሪን ደንበኛ ተሽከርካሪ በቆመበት በመግጨት ጉዳት በማድረሱ ተጠሪ ብር 29,478.25 ወጪ በማድረግ የደንበኛዉን ተሽከርካሪ በማስጠገኑ ይህ ገንዘብ እንዲተካለት በአመልካች ላይ የመሰረተዉ ክስ እንደሆነና የክልሉ ፍርድ ቤቶች አመልካች የጉዳት አድራሹ ብስክሌት ባለቤት በመሆናቸዉ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍሉ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2081/1ን በመጥቀስ መወሰናቸዉን ከግራ ቀኝ ክርክርና ከክልሉ ፍርድ ቤቶች ዉሳኔዎች ይዘት ተረድተናል፡፡

በፍ/ብ/ሕግ ከቁጥር 2086 እስከ 2089 ድረስ ባሉ ድንጋጌዎች አንድ ሰዉ ጥፋት ሳይኖርበት ኃላፊ የሚሆንባቸዉ ሁኔታዎች(Strict Liability) ተዘርዝረዉ ተደንግገዋል። የስር ፍርድ ቤቶች አመልካችን ኃላፊ ያደረጉትም አመልካች ጉዳት አደረሰ የተባለዉ ብስክሌት ባለቤት ናቸዉ በሚል ሲሆን መሰረት ያደረጉትም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2081/1 ስር የተደነገገዉን ነዉ። በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2081/1 ስር የአንድ መኪና ወይም አንድ ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት የሆነ ሰዉ አደጋዉን ያደረሰዉ ይህን መኪና ወይም ይህን ባለሞተር ተሽከርካሪ ለማንቀሳቀቅ ወይም ለመንዳት ባልተፈቀደለት ሰዉ ቢሆን እንኳ መኪናዉ ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪዉ ባደረሰዉ ጉዳት ኃላፊ የሚሆነዉ ባለሀብቱ እንደሆነ ተደንግጓል። በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጥፋት ሳይኖር ኃላፊ ለመሆን መሟላት ያለበት ዋና መስፈርት ኃላፊ የሚደረገዉ ሰዉ አደጋ ያደረሰዉ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት መሆን አለበት የሚለዉ ነዉ። ስለሆነም "ብስክሌት" መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ሊባል የሚችል መሆን አለመሆኑን መለየት ያስፈልጋል።

በተሽከርካሪ መለያ መመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 681/2002 አንቀጽ 2/1) ስር እንደተደነገገዉ ብስክሌት ማለት በሚነዳዉ ሰዉ ኃይል እየተንቀሳቀሰ የሚሄድ ተሽከርካሪ ሲሆን በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2/4 ላይ እንደተመለከተዉ ባለሞተር ተሽከርካሪ ማለት ደግሞ በመካኒካል ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል በመንገድ ላይ እየተንቀሳቀሰ የሚሄድ ተሽከርካሪ እንደሆነ የተሰጠዉ ትርጉም ያሳያል። በዚህ አዋጅ "መኪና" ተብሎ ለሚታወቅ ቃል ትርጉም ባይሰጠዉም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2081/1 ስር በአማርኛዉ የሕጉ ቅጅ ላይ መኪና ተብሎ የተገለጸዉ በሕጉ የእንግሊዝኛ ቅጅ ላይ " machine " ተብሎ የተገለጸ ሲሆን መኪና የሚለዉ ቃል በአቢሲኒካ መዝገበ ቃላት እንደተተረጎመዉ *"መኪና ማለት "macchina" ከሚለዉ የጣሊያንኛ ቃል የተወሰደ ቃል ሲሆን፣(ወይም አዉቶሞቢል፣ ተሽከርካሪ) ከሥፍራ ወደ ሥፍራ በመንኮራኩር ላይ በሞቶር የሚነዳ ተንቀሳቃሽ አይነት ነዉ።"* (በhttps://dictionary.abyssinica.com/ ይገኛል) ከዚህ የምንረዳዉ መኪና ከብስክሌት የተለየ በሞተር ኃይል የሚነዳ(የሚነቀሳቀስ) መሳሪያ መሆኑን ነዉ።

ከላይ እንደተገጸዉ ብስክሌት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2081/1 ስር መኪና እና ባለሞተር ተሽከርካሪ ተብለዉ ከተገለጹት የተለየ በሚነዳዉ ሰዉ ኃይል እተንቀሳቀሰ የሚሄድ ተሽከርካሪ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2081/1 ስር የሚሸፈን ባለመሆኑ በብስክሌት ለደረሰ አደጋ የብስክሌቱ ባለቤት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2081/1 ስር በተደነገገዉ መሰረት ጥፋት ሳይኖርበት ኃላፊ ሊሆን አይችልም።እንዲሁም አንድ ሰዉ ጥፋት ሳይኖርበት ኃላፊ ስለሚሆንበት ሁኔታዎች(Strict

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍ ር ዮ አ ፈ ጸ ጸ ምዓ ለ ማአ የ ገ ለ ግል ም!

Liability) በፍ/ብ/ሕግ ከቁጥር 2086 እስከ 2089 በተደነገጉ ድንጋጌዎች ስር የብስክሌት ባለቤት የሆነ ሰዉ ጥፋት ሳይኖርበት ኃላፊ ሊሆን እንደሚችል በግልጽ አልተደነገገም፡፡

በሌላ በኩል በብስክሌት አደጋ ከደረሰ የብስክሌቱ ባለቤት ኃላፊ ሊሆን የሚችለዉ በምን ሁኔታ ነዉ ለሚለዉ ነጥብ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር እንደመረመርነዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2087 ሌሎች ነገሮች በሚል ርእስ ስር የአንድ ነገር ባለቤት ወይም ጠባቂ የሆነ ሰዉ ራሱ ጥፋት ካላደረገ ወይም በራሱ ኃላፊነት ዉስጥ የሚተደደር ሰዉ ካላጠፋ በቀር ከዚህ በላይ ባሉት ቁጥሮች (በፍ/ብ/ሕግ ከቁጥር 2086 እስከ 2089 ለማለት ነዉ) ከተመለከተዉ አስተያየት ዉጭ በሆነ ጉዳይ በኃላፊነት እንደማይጠየቅ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በላይ እንደተገለጸዉ በፍ/ብ/ሕግ ከቁጥር 2086 እስከ 2089 ስር በተደነገጉ ድንጋጌዎች ስር የብስክሌት ባለቤት የሆነ ሰዉ በብስክሌቱ ለደረሰ አደጋ ጥፋት ሳይኖርበት ኃላፊ የሚሆንበት ሁኔታ ያልተደነገገ በመሆኑ የብስክሌቱ ባለቤት ኃላፊ የሚሆነዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2087 መሰረት ጥፋት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ብቻ ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተዉ ንብረትነቱ የአሁን አመልካች የሆነ ብስክሌት በሌላ ሰዉ ሲሽከረከር የደንበኛዉ ተሽከርካሪ ቆሞ ባለበት ገጭቶ ጉዳት ማድረሱን በመግለጽ አመልካች የብስክሌቱ ባለቤት በመሆናቸዉ ብቻ በደንበኛዉ ተሽከርካሪ ላይ የደረሰዉን ጉዳት ለማስጠገን ያወጣዉን ወጪ አመልካች እንዲተኩላቸዉ እንዲወሰንለት ነዉ፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ያየዉ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2081/1ን በመጥቀስ የብስክሌቱ ባለቤት በመሆናቸዉ አመልካችን ኃላፊ በማድረግ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየዉ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ዉሳኔዉን ተመሳሳይ ድንጋጌ በመጥቀስ በማጽናት ወስኗል፡፡ሆኖም ከላይ እንደተገለጸዉ ብስክሌት መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ስላልሆነ አመልካች የብስክሌቱ ባለቤት በመሆናቸዉ ብቻ ያለጥፋት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2081/1 መሰረት ለደረሰዉ ጉዳት ኃላፊ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2081/1 የብስክሌት ባለቤት ኃላፊ የሚያደርግ ድንጋጌ አይደለም፡፡ እንዲሁም በፍ/ብ/ሕግ ከቁጥር 2086 እስከ 2089 ስር በተደነገጉ ድንጋጌዎች ስር የብስክሌት ባለቤት የሆነ ሰዉ በብስክሌቱ ለደረሰ አደጋ ጥፋት ሳይኖርበት ኃላፊ የሚሆንበት ሁኔታ ያልተደነገገ በመሆኑ የብስክሌቱ ባለቤት ኃላፊ የሚሆነዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2087 መሰረት ጥፋት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ብቻ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል የክልሉ ፍርድ ቤቶች አመልካች የብስክሌቱ ባለቤት ናቸዉ በሚል ብስክሌት መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለሆነበት ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2081/1ን

በመጥቀስ አመልካችን ኃላፊ በማድረግ አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንዲከፍሉ መወሰናቸዉ አመልካች በሕግ ከተደነገገዉ አግባብ ዉጪ ኃላፊ እንዲሆኑ የሚያደረግ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ በመ/ቁጥር 0125071 ላይ በቀን 29/10/2010 ዓ/ም እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 02-19550 ላይ በቀን 17/04/2011 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት የፍርድ ዉሳኔዎች በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. ግራ ቀኝ በዚህ ፍርድ ቤት ደረጃ ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

- የዚህ የፍርድ ዉሳኔ ግልባጭ ለክልሉ ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- ዉሳኔዉ ይታተም ዘንድ ለፍርድ ቤቱ ጥናትና ሕግ ክፍል ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ፤መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

-

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

አ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርዮአፈጸጸምዓለማአ የግ ለግልም!